# ይቅርታ እንጠየቅ ጎበዝ!

**ሀማ ቱማ**

ፖለቲካና ቧልትን በማገናኘት አንዳንዴ ጫር ጫር ባደርግ ከረር ያሉ ውግዘቶችን ተቀብዬ ነበር፡ በራስ ላይ የመሳቁ ጉዳይ ለብዙዎች የሚጥም አይደለም። በእኔ ተመክሮ ደግሞ ራሳቸውን አሳብጠ ው ከትችትም በላይ የሚያደርጉት ሳይውል ሳያድር ሂደታቸው ወደ ክሽፈት መሆኑ አይቀሬ ነው። ፖለቲካ ቧልት አይደለም ነገር ግን በድርጅቶችና ፖለቲከኞች ላይ የመሳቅ መብታችን መጠበቁ አስፈላጊ ነው። ብዙ መከራ አብረን ያሳለፍነው ብርሃነ መስቀል ረዳ ለምሳሌ ስለራሱ ያለው ግምት በጣም የተጋነነ ነበርና ፤ በታሪክ መድረክ ልዩ ቦታ አለኝ ባይ ነበርና ይህን እውን ላድርግ ብሎ ሲነሳ ከሕዝብ ጎራ ለቆ ወደ አንጃነት/ባንዳነት መደባለቁ ግድ ሆነ። ከሀገራችን ስንወጣ ሌሎቻችን መሰረተ ትምህርት እንኳን ለመጨረሳችን ማስረጃ ወይም ምንም መታወቂያወረቀት ያልያዝን ስንሆን ብርሀነ መስቀል ግን በጠበቃ ቦርሳ ታሪኩን አሳምሮ ለመፃፍ የሚያመቸውን ሰነድ ሁሉይዞ ነበር። በታሪክ ቦታውን አዋቂ ወይስ ግብዝ? ለማንኛውም ይህ ለራሱ የሰጠው ግምት ወደ አንጃነት መክተት ብቻ ሳይሆን በደርግ ወደ መያዝና መገደልም አመራው።ራስን ማሳበጥና ከድርጅ ትም ከህዝብም በላይ ማድረግ መጨረሻው የማያምር ፍንዳታ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። በተለይይህ ለግል ከፍተኛ ቦታ የመስጠቱ አባዜ ከችሎታም ከድፍረትም ጋር ያልተያያዘ ከሆነ ደግሞ መሳቂያ መሳለቂያ ያደርጋል። አንቱ በሉኝ ባዮች ምንኛ መናኛ መሆናቸውን አይተናል፤ እያየንም ነው።ለዚህም ነበር እምባጮን ለታቦት መቁረጡ ይቁም፤ጣዖት ጠረባውም አይጠቅምም ለማለት የበኩሌን ሞክሬ የነበረው።

ወደ ተነሳሁበት ርዕስ ለመመለስ ይቅርታ እንጠየቅ ያልኩት የሀገራችን ልምድ ሆኖ ያጠፋ በራሱ ይቅርታ መጠየቅ የማይታሰብ በመሆኑም ነው። ያጠፉ እንኳን ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ሊጠይቁ ቀርቶ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሌላውን/ሰለባቸውን/ ይከሳሉ። በሀገራችን ታሪክና በዓለም ደረጃም አሰቃቂ የተባለውን የቀይ ሽብር ወንጀል የፈፀሙ አረመኔዎች ዛሬ በስደት ዓለም ሆነው ኢሕአፓን ሲወነጅሉና ሲከሱ እየሰማን መሆናችን በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ወያኔም ነጋ ጠባ ሲዋሽ፤ሲቀጥፍና ሲገድል እየታየ በግፍ ያሰራቸውን ራሳቸውን ይቅርታ ይጠይቁኝ ሲል ታዝበናል። ያጠፋውን ደግፈው የተበደለውን ይቅርታ ጠይቅ ባዮችም አስታራቂ ሽማግሌዎች ተብለው ተቀልዶብናል።የተገላቢጦሽ ሆኗል ነገሩ ሁሉ ብንል ማጋነን አይሆንም። ከዚህ ቀደም በፖለቲካው መስክ በመብረቃዊ ፍጥነት ዘው ብለው ሳይውል ሳያድር ግራ ቀኙን በቃላት ፍላፃ መዘረ ር የሞከሩትን አደብ ግዙ ብለን በመከርን፤ በአስኮላ የፈረንጅ ትምህርት ዶክተርነቱ የፖለቲካ ሊቅ አያደርግም ብለን ባሳሰብን፤ ተደራጀን ብለው ከወያኔ ሰርጎገቦች ጋር ሲተቃቀፉ ጠንቀቅ የሀገር ልጅ

ብለን ድምፅ ባሰማን፣ ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ነን ብለው ጭፍን ደጋፊን በአደባባይ ጫማ ሲያስሙ ይህ አፄያዊ ክስተት አይበጅም፣ ያስገምተናል ባልን ወዘተ በድርጅቶች ጉዳይ ጣልቃ ገባችሁ፣ ወይዘሪት መሪያችንን በክብረ ነክ ደፈራችሁ፣ በተማሪ ሁሉ ቀናችሁ ወዘተ በሚል ተወግዘን ነበር:: ውግዘቱ ደግሞ በተለይም በዚህ ፀሀፊ ላይ የከፋና መረን የለቀቀ ነበር:: የፈረደበት ኢሕአፓም ቢለምደውም እንኳን ነጋ ጠባ መወቀጡና በተለይም ትላንት በቀይ ሽብር ሳይቀር ሲጨፈጭፉት በነበሩትም መዘለፉና መጠቃቱ የቀጠለ ነው::

በ66ቱ አብዮት ወቅት አፋዊ ዴሞክራሲ ሀገርን ሊያጣብብ ሲነሳና በተለይም ኢትዮጵያ ትቅደም አለምንም ደም እያሉ ሀገሪቷን በደም ሊያጥለቀልቁ ሲዘጋጁ ኢሕአፓ የዚህ የመኮንኖች ቡድን አዝማሚያ ሳይሆን የማይቀረው መጨረሻው ፋሺስታዊ ነውና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም ብሎ ጥሪ አሰምቶ ነበር:: የለም ስህተት ነው ያሉና አልፎም ያንን ቁርፋዳ ቡድን የደገፉት ደግሞ በሕዝብም ላይ በራሳቸውም ላይ ፋሺስታዊ ዶፍን አወረዱ:: የወያኔ ድርጅትም ራሱን ኢሕአዴግ በሚል ቁርበት ሸፍኖና ሀገርን ለባዕዳን ሽጦ ወደ ስልጣን ሲጓዝ ኢሕአፓ የዚህን ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ይዘትና መጨረሻ በማስረዳትና በተለይም በጫካ በነበረው ፍኖተ ራዲዮ አማካይነት ቅስቀሳ በማካሄድ ዜጎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ከማሳሰቡ ሌላ በኅበዝአለቃ ተደራጅቶ መታገልም ወሳኝ መሆኑንም ገልፆ ነበር:: መግለፅ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ እርምጃዎችንም ወስዶ እንደነበር የታወቀ ነው:: ይህም በብዛት አልተደመጠም:: ልጆቼ ናቸው ባዮች፣ ጊዜ እንስጣቸው ባዮች፣ መቸም ሳይዋጉ ጦርነት ሰለቸን ባዮች፣ ወያኔን መቃወም ፀረ ትግሬ መሆን ነው ባዮች፣ ወሎና ጎንደር መሬቱ ሲወሰድ ምን አለበት ባዮች፣ወያኔን አድምጠው በብሄረሰብ ደረጃ መደራጀትን የተከተሉ ብዙዎች፣ወያኔ እነ ኢሕአፓን ከሱዳንና ሌሎች ተባብሮ ሲያጠቃ ምን አገባን ባዮች መድረኩን አጣበው ለወያኔ ጊዜ ተሰጠው:: እኩይ ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ዕድል ተሰጠው:: ባለፈው የ 97 ግንቦት ምርጫ ወቅትም ኢሕአፓ የምርጫው ህግና ቦርድ ካልተለወጡና የሚገኝን ድል ማስከበሪያ ጉልበት ወይም መንገድ ከሌለ ወያኔ ቢሸነፍም ከስልጣን አይወርድም ብሎ ቢጮህም በጊዜያዊ ሆይ ሆይታ ዕይታቸው በአጭሩ የተወሰነባቸው በዙና ያው በተባለው መሰረት ሽንፈት የደረሰበት ወያኔ በጭፍጨፋ በስልጣን ቀጠለ :: ቀጥሎም ያለው አማራጭ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን ማፈንናማሰር ነውና ጠንቀቅ እንበል ሲል ኢሕአፓ ቢያስጠነቅቅም አሜሪካ አይፈቅድለት ምና አያስረንም ብለው የተሞኙ ነበሩ:: ካለፈው ታህሳስ በፊት ኢሕአፓ የወያኔ አገዛዝ ለሱዳን መሬታችንን ሊለግስ ነው ብሎ ማጋለጡና ዋሸህ ተብሎም መወገዙ የሚታወስ ነው::

በግ እንኳን ሲደባለቅ ባ ይላል ተብሎ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ከሕዝብ አቅዋም በተፃረረ መንገድ የነጎዱት ሁሉ በ "ባ" ፈንታ ንስሀ ገብተው ወይም አጠፉን ብለው ሕዝብን ቢደባለቁ ሊመረጥ ይገባው ነበር፡፡ ይህ ግን አልሆነም፡፡ በታሪክ ምርመራ ሙትን መውቀሱ የማይቀር ነውና ለጣሊያን ወራሪ የሰገደና ያገለገለውን ባንዳ ሁሉ የሾሙት አፄ ኃይለስላሴ ተጠያቂ መሆናቸው መጠቀስያለበት ነው፡፡ ለሀገሩ መከራ የተቀበለው አርበኛ ወይ ሲሰቀል ወይ ሲገለል ምድረ ባንዳ ወደ ስልጣንና ወደ መድረክ ወጣ፡፡ ጣሊያን የሰጣቸው ሹመት ፀደቀላቸው፡፡ የአዜቧን አጎት፣ የመለስን አያት፣የተሾሙ የሰሜን አስካሪዎችንና ባንዶችን ይጠቅሷል፡፡ ይህ መጥፎ ልምድ ማለትም የሞተልሽ ሳይሆን የገደለሽ በላው ልምድ ያስከተለው መዘዝ ደግሞ ዛሬም አብሮን አለ፡፡

አፄውን ሲያገለግሉ የነበሩ፣ አፄው ምን አጠፉ ባዮች፣የሚታገሉትን ያወግዙ የነበሩ ደግሞ ደርግ ለስልጣን ሲበቃ ከመ ቅፅበት ማርክሳዊ ሌመሂናዊና ተራማጅ ሆነው ለደርግ አገልጋይና ታማኝ ነን አሉ፡፡ ለከፍተኛ ስልጣንም በቁ፡፡ ፋሲል ናሆም ማለቱ ብቻ ዝርዝሩን አይጨርሰውም፡፡ ለለውጥ የታገሉት ደግሞ ተጨፈጨፉ፡፡ ይህ ምፀት ደግሞ በወያኔም ጊዜ ተደግሟል--ፋሲል ናሆሞችም የአዲሱ አገዛዝ አማካሪና ሚመሂስቴሮች ሆነዋል፡፡ የፈረደባቸውም ተገድለዋል፣ታስረዋል፣ተሰደዋል፡፡ በዚሁ በሚገባ ሊጠና በሚገባው የታሪክ ሂደት ውስጥ በአብዛኛው ለሀገሩና ለሀቅ የቆመው ሲጠቃና ሀገርና ሕዝብን የሸጠው ደግሞ ቦታው ትቢያ ሳይሆን ወደ ክብር እየሆነ በመቀጠሉ ትውልድ የሚቀስመው ትምህርት ጤነኛ አልሆነም፡፡ በካናዳ አንድ ከተማ በተደረገ ስብሰባ የተገኙ ወጣቶች መሀል አንዱ "ጋሼ የምትለው ይገባናል--ግን ያንተ መንገድ ብዙ ችግርን ያስከትላል ለአንተስ ምን በጀህ?" ካለ በኋላ የአንድ የደርግ ባለስልጣንና ዛሬ በአሜሪካ ተንደላቆ የሚ ኖር ግለሰብን ስም ጠርቶ "አንተን ለሀገር እንቁም ስትል ስንት ዓመት ያሳለፍከውንና እሱን ሳይ ማን ተመቸው አለፈለት ብዬ ስጠይቅ መልሱ አንተ ነህ የሚል አይደለም" ሲል ነግሮኛል፡፡ አልፈረድኩበ ትም፡፡ ኢትዮጵያ ምን ትሰጠኛለች የሚል ከሆነ ጥያቄው ሀገሪቷ ላይ ተንፈራጦ የሚኖርባት የተዋደ ቀላት ሳይሆን ያወደቃት ነው፡፡ ሀቅንና ኢትዮጵያዊነትን ተከትሎና በጣም ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሎ የታገለው ኢሕአፓ ሳይሆን ራሱንም ሀገርንም ለባዕድ የሸጠው ወያኔ ቤተ መንግስት በመግባ ቱ ብልህ ያሉትና የተነጠፉለት ጥቂቶች አይደሉም፡፡ የሩቁ ይቅርና ትላንት ለወያኔ ያደሩና የሕዝብ ን ትግል ሲያንኳስሱና ሲጎዱ የነበሩት በሆነ ምክንያት ከመለስ ዜናዊ ሲጣሉ በቀጥታ ወደ ሕዝብ ጎራ ገብተው ከእኛ በላይስ ሀገር ወዳድ ታጋይ ማን ተገኝቶ ብለው ሊቧርቁ በቁ፡፡ ጥፋቱ ደግሞ ጥፋታችሁን እመኑ፣ከሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ ሳይል አቅፎ ተቀብሎ ጭንቅላቱ ላይ የሚያስቀምጣቸ ው የሕዝብ ጎራ ነኝ ባዩ ነው፡፡እነ ፀጋዬ ገብረመድህን ደብተራውን ደብዛ ያጠፋው፣ እነ ገለብና መስከረምን ያስገደለው፣ጦርነት እንሰራባችኋለን ብሎ ሕዝብ ላይ የደነፋው ግለሰብ ከመለስ ቢጣላ የሀገር ጀግና ብለው በራሳችን ላይ ሊጭኑት የለመደባቸው ብቻሳይሆኑ ደም ረጋጭ አንጃዎችም

ሲሞክሩ አልታዘብንም? በጎጥ ተደራጅቶ የወያኔ ምክትል ሚመሄስቴር የነበረው ተሳስቼ ነበር ሳይል የህብረት ግንባር ጥሪቶች አባወራ ሆኖ ከርሞ ያው ሕዝብን ከዳ፡፡ ሀሰን አሊና አልማዝ መኮ? የወያኔ አገዛዝን ከፋፋይ መስመር በተለይም በአማራው ሕዝብ ላይ ሲገፋ የነበረው፣ እነ መለስን ልጆቼ ብሎ አቆላምጦ ተቃዋሚዎችን የዘለፈው፣ የሕዝብን ወሳኝ ትግል ከባዕዳንና ከነበረከት ስምዖን ጋር ሆኖ መቀመቅ የከተተውና ሌሎችም መሰሎቻቸውም ዛሬ የሕዝብ ጎራ አባወራና መሪ ነን ብለው ሲወራጩ እያየን ነው፡፡ የቀይ ሽብር ነፍሰ ገዳዮችም ማፈር ብቻ ሳይሆን እስሩ ቢቀር ገዳም መግባት ሲገባቸው በተቃራመሄው የፖለቲካውን መድረክ ይዘው የፈረደበትን ኢሕአፓን (ብይ ስንጫወት እንል እንደነበረውም በስፖንዳም እኔንም) ሲወነጅሉና ሲሰድቡ ደከመን የሚሉ አልሆኑም፡፡

ሀገርን የማስከበርና የሕዝብን መብት የማረጋገጥ ፖለቲካና ትግል አንድን ጮሌ ወደ ስልጣን ለማድረስ ከሚደረግ ግብግብ ጋር የተመሳሳለ አይደለም፡፡ ሕዝባዊው ትግል ሀቀኝነትን፣ፅናትን፣ ቀና ዓላማንና ያልቆሸሸ ታሪክን ይጠይቃል፡፡ ለአድርባዮች እርያ የሚንከባለልበት ጭቃ ሊሆንላቸው አይችልም፡፡ ትላንት ከሕዝብ ጠላቶችና ከሀገር ጠይ ባዕዳን ጋር አብረው በሕዝብ ላይ ሲጫወቱና ሀገርን ሲጎዱ የነበሩ ዛሬ አለምንም ንስሀ የሕዝብ ጎራ አባል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህንን መፍቀድ ማለት የራስን ሕዝብ ትግል ማቆሸሽ ማዳከም ማለት ነው፡፡ ሕዝብ መሪ ብሎ የሚሰይማቸው የሕዝብ መሪ ሊኖረው/ሊኖራት የሚገባውን ፀጋና ችሎታ የሌላቸው ከሆኑ ሕዝብራሱ በራሱ ትግል ላይ ቀልዷል ማለት ነው፡፡ ምንኛ ቢያሞግስና ቢያሞካሻቸው ትግሉ የሚጠይቀውን ወኔና ፅናት፣ ችሎታና ሀገራዊ አስተሳሰብን ይዘው አይገኙም፡፡ ለዚህ ደግሞ ምሳሌ መጥቀሱ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ የራሳቸውን ፍርሀት ያልተቆጣጠሩ የምልዓቱ ሕዝብን ወኔ ሊቀሰቅሱና ሊመሩ የሚችሉበት ተዓምር የሚታይ አይደለም፡፡ በረጅሙ ትግል የገበየነው ተመክሮ፣ ከራሳችን ስህተትና ብዥታ ያገኘነው የደም ዋጋ የጠየቀ ዕውቀት ደግሞ የፈሪ ፈታውራሪ፣ የአድርባይ ሕዝብን ነፃ አውጪ፣ የጠባብ ብሄረተኛ ሀገር ወዳድ፣ የአንጀኛና በታኝ ታጋይ፣ የወያኔ ኢትዮጵያዊ አለመኖሩን በሚገባ አስጨብጦናል፡፡ ዛሬም ከስህተት ነፃ ነን ባንልንም ከመ ማሞ ቂሎ ያለፈውን ስህተት ልንደግም ደግሞ የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ነጋዴ (ወይም የነጋዴ ልጅ ) ይመስል ትግልን በተራ ትርፍ--ኪሳራ ለመተመንም መነሳት አሳፋሪና ውጤቱ የማያምር ነው፡፡ ጣሊያን ሀገርን ወረረ፣ ዘመናዊ መሳሪያ ነበረው፣ ሀገር ወዳዶች በሚኒሽርና በጦር ጋሻ ተጋፈጡት ("እብደት!")፣አንድ ሚሊዮን ሰው አለቀ--ክስረት! ተማሪዎች አለ አቅማቸው ግዙፉን የአፄ ስርዓት ታገሉ፣ብዙ ተጎዱ---ክስረት፡፡ ኢሕአፓና ሕዝብ ለደርግ አልገዛም ብሎ ተዋደ ቀ፣ በቀይ ሽብር ተፈጀ --ኪሳራ፡፡ የሕዝብ ትግል ከቀጠለ አገዛዙ ሊጎዳን ይችላል ብለን ከአሜሪካኖ ችና እንግሊዞች ጋር ተወያይተን የሙት ከተማ አድማውን አከሸፍነው--ትርፍ፡፡ በዚህ መልክ ትግል

ከተመዘነ ትግል መቸም የሚካሄድ አይሆንም። ይህ ያልገባቸው ነቃን ባይ አስመሳዮች ግን ትርፍ ኪሳራ ብለው ሁሌም እጅ መስጠትን፣ መንበርከክን፣ እየተገዙ መበርከትን በትርፍ እየፈረጁ ወሳኝ ትግልን ማጅራት ይመታሉ። ቢያንስ ሊወቀሱ ሲገባ ብልህ ተብለው ሊወደሱ ይፈልጋሉ፣አወዳሾችም የጠፉ አይደሉም። ዛሬ በሚታየው የገበያ መሰል ግርግርና ፖለቲከኛ ነን ብለው ንግድ የተያያዙ በመብዛታቸው ግልፅ ሆኖ ባይታይም ፖለቲካ ንግድ አይደለም። እምነትን ይጠይቃል፣ መርህ ሊመራው ይገባል። በየመንገዱ መርህና እምነትን ለድርድር ማቅረብም ውርደት ነው። ይህ ለድርጅት ቁሪስቶችና ነጋ ጠባ መርህ ያሉትን ለሚቀይሩና ለሚክዱ እንግዳ ሊሆን ቢችልም ሀቅ ነው። ሀገርን ለማዳን መደረግ ያለበት ትግል እናሸንፋለን ወይስ እንሞታለን በሚል የሚተመን አይደ ለም። ሀገርን ለማዳን መዋጋት የግድ ነው። አሸነፍን ወይም መከራው በዝቶ ተጎዳን ትግል የግድ ነው ና ማከሄድ አለበት። ትርፍ ኪሳራ እዚህላይ ቦታ የለውም። መስዋዕትነት ከፍሎ፣ለቀጣዮች አርአያነ ትን አስመዝግቦ ማለፍም ትግል ነው። አለመታገል ነው ሁሌም ኪሳራ! አንድ የክህደትና የፍርሀት ምሳሌ የሆነ ግለሰብ ሕዝብን ከድቶ ለወያኔ ሲያድር ብልጥ ልጅ የተሰጠውን ተቀብሎ ተጨማሪ ይ ጠይቃል ዓይነት ንግግር አሰምቶ ነበር። አድርባይነት ሲራቀቅ? የትርፍ ኪሳራ ተመን? የከሰረ ፖለቲካ። አሳፋሪ አቅዋም።

ሀቁ ተነገረ በሚል ተናጋሪውን ያወገዙ ሁሉ ዛሬ ተገልብጠው ያወገዙትን ሀቅ ሲሉ ጎበዝ በመጀመሪያ ይቅርታ ጠይቁን እንጂ ብንል ሲያንስ ነው። መጠየቁ ተገቢ ነው።ከሂሳብ ማወራረድ ባሻገር እያድበሰበሱ ማለፍን ይገታል። ከወያኔ የተቃቀፈ ክርፋቱን ሳይታጠብ ሕዝብን ሊያቅፍ አይችልም የሚለውን መልዕክት ያዳርሳል። ኢትዮጵያ ለሞተላት እንጂ ለገደላት መሆኗንም ማቆም አለባት የሚለውን ወቅታዊ አቅዋም ያነግሳል። ከወንድምና እህቱ፣ ከጓድ ገዳይ ጋር መተቃቀፍ ሀጢያት መሆኑን ያስተምራል። ወንጀለኛ ከተሸለመ ወንጀል እንዲስፋፋ ይረዳል። ባንዳና ሕዝብን ገዳይ ምንም ካልደረሰበት፣ ይቅርታ እንኳን መጠየቅ ሳይገደድ ከሕዝብ ጎራ ከተደባለቀ የቀጣይ ዙር ነፍሰ ገዳዮችንና ከሀዲዎችን የሚያበረታታ ይሆናል። መታወቅ ያለበት መሰረታዊ ጉዳይ ደግሞ ከሕዝብም ከሀገር ጠላትም ወዳጅ ሊኮን አለመቻሉን ነው። የእንቻቻል ሰበካ በዚህ አይሰራም። የማንዴላነት ምክርም አለቦታው ነው። የደቡብ አፍሪካ ተመክሮ ዛሬ በጥያቄ የገባ ከመሆኑ ሌላ የዕርቁ ፖለቲካ የነጩ ዘረኛ አገዛዝ ከወደቀ በኋላ የተካሄደ ነው። ወያኔ በስልጣን እያለ ከወያኔ ጋር ዕርቁ ሊካሄድ የሚችል አለመሆኑ ታይቷል። ዛሬ ለወያኔ በርከክ ብለን፣ አገዛዙን ተቀብለን እንታረቀው የሚሉ ሁሉ የሕዝብን ጎራ የለቀቁ አድርባዮች መሆናቸው አከራካሪ አይደለም። ይህ ሁሉ ግልፅ ከሆነና አድርባዮቹ ያስፋፉት የውዥንብር ጭጋግ ከተነነ ይቅርታ እንጠየቅ ብለን በሕዝብ፣በድርጅትና በግለሰብ ደረጃም መጠየቃችን ፍትሃዊና ተገቢ ይሆናል።

- ጨቋኙን የአፄ አገዛዝ ልንታገል ስንነሳ አፄው ያጠፉት የለም፣ ጠገባችሁ ያሉ፣ ትግላችን ን ያወገዙና ዛሬም በመድረክ ተቃዋሚ ነን ሊሉ የተነሱት ላለፈው ጥፋታቸው ይቅርታ ሊጠይቁን ይገባል::
- የምርጥ መኮንኖች ቡድን ለስልጣን ሲበቃና ሕዝብ ከኢሕአፓ ጎን ሆኖ ትግሉን ሲያፋፍ ም ከደርጉ ቆን ቆመው የሕዝብን ትግል ያደናቀፉት ከሕዝብ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል::

- ፋሺስቱ ደርግ ጋር ሆነው ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ያካሄዱ፣ ድርጊታቸውን የደበቁ ቀልቤሳዎች፣እርገጤዎች በየአከባቢው ግፍ የፈፀሙ ወንጀለኞች ሁሉ ከሕዝብም ከኢሕአፓም ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው::
- በአሶሳ ሕዝብን የጨፈጨፉ ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው::

- ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን መስርተው፣ ትግራይ ትገንጠል የሚል መርህ ግብር አውጥተው ፣ የትግራይ መሬት ወልቃይት፣ ጠገዴንና የወሎ መሬትንም ያጠቃልላል ያሉና በኢሕአ ፓና በሕዝብ ላይ ጦርነት ያወጁና ደም ያፈሰሱ፣ የትግራይ ወጣቶችን በጠመንጃ የቀየሩ ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው::

- ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ ይህንን ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ደግፈው የሕዝብን ትግል ያደናቀፉ፣ እነ መለስን ልጆቼ ያሉ፣ በወያኔ ቦይ ጠባብ ሆነው ተደራጅተው የፈሰሱ፣ የአማራውን ኢትዮጵያዊነት በጥፋት ፈርጀው ያወገዙና መፅሀፍ ብጤ የፃፉ፣ወዘተ ሁሉ ዛሬ ከሕዝብ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል::
- ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆነው በሕዝብ ላይ ወንጀል የፈፀሙ፣ሀገርን የከፋፈሉ፣ የገደሉ፣ የታሰሩትን ደብዛ ያጠፉ፣ጦርነት እንሰራባችኋለን ብለው የደነፉ፣ በደኖና አርባጉጉን በደም ያጠቡ፣ ወጣቶችንና ምዕመናን የፈጁና ያስፈጁ ከሕዝብ ጎራ ከመግባታቸው በፊት ከሕዝብ በይፋ ይቅርታና ምህረትን መጠየቅ አለባቸው::

ከወንጀለኛ ጎራ ወደ ሕዝብ ጎራ ሽግግሩ በዓይና አውጣነትና በደም ረጋጭነት ሳይሆን በንስሀና ሕዝብን ይቅርታ በመጠየቅ ብቻ ነው:: ሌላ መንገድ የለም:: ሌላ መንገድ ሊከፈትና ሊፈቀድ ከቶም መቸም አይገባም:: ከዚህ በላይ በወንጀለኛ ደረጃ ያስቀመጥናቸውና ሕዝብ የሚያውቃቸው ጉዶች ዛሬ በየድርጅቱ ተሰግስገው፣ ራሳቸውን ተቃዋሚ ብለው ሰይመውና ቅንጣትም የይቅርታ ድምፅ ሳያሰሙ፣ይባስ ብለው ዛሬም ታጋይ

ድርጅቶችና ሀገር ወዳዶችን ሊያጠቁ ሲፍጨረጨሩ በዝምታ ልናይ አይገባም፡፡ ከነፍሰ ገዳዮችና ሀገር ሻጮች ጋር መተቃቀፋን በብልህነት ወይም ስልጡን ፖለቲካ ደረጃ ሊፈርጁ ደፋ ቀና የሚሉትም ህሳዊ መሲህና ትግል ገዳይ መሆናቸውን--አውቀው ሰሩት አላደረጉት-- ሊነገራቸው ይገባል፡፡ ይህን በዚህ ለጊዜው ቋጭተን ወደ ሌሎች ይቅርታ አስጠያቂ ጉዳዮች ስንመለስ ደግሞ ሌሎች የምናነሳቸው ይኖራሉ፡፡

- ህብረቱ እንዳይመሰረት የዘመቱና ሲመሰረትም ይህን ህብረት ሊያፈርሱ የጣሩት ሁሉ ይቅርታ መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡
- በምርጫ ከመሳተፍ በፊት የምርጫው ህግና ቦርድ ይቀየር ብሎ መጠየቁና በዚህም መፅናቱ ወሳኝ ነው ስንል አሌ ያሉና አለምንም ለውጥ በምርጫ እንሳተፋለን ያሉና ትግሉን ወደዱም ጠሉም የገደሉ ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው፡፡
- ያን ታሪካዊ የሕዝብ ንቅናቄ ያሽመደመዱ፤ ከባዕዳን ተመሳጥረው የሕዝቡን ትግል ያኮላሹ፤ሕዝብን ከድተው ከወያኔ ተሰልፈው ፓርላማ የገቡ፤ ድርጅቶችን የከፋፈሉ፤ የትግል ወንድም እህታቸውን የከዱ ከሕዝብ ጎራ ዳግም ዘው ከማለታቸው በፊት ይቅርታ መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡

ብለን ነበር ማለቱ ብዙ ባይስብም ዛሬ የሆነውን ትላንት ሊሆን ይችላል በማለታችን ያወገዙን ዛሬ ወደዚህ ጎራ ከመጡ ዘንዳ ጎበዝ ተሳስተን ዘባርቀን ነበር ብሎ ማመን ይኖርባቸዋል፡፡ የማሸነፍ የመሸነ ፍ ጥያቄ አይደለም--ታሪክን የማስተካከል እንጂ፡፡ ከዚህ ሌላ የተቃዋሚ ጎራ ድርጅቶች ድክመታቸ ው ሲጠቀስ ክብረ ነክ ተደርጎ በመወሰዱ ከድክመት ተምሮና አርሞ ወደፊት ተስተካክሎ መሄድ አልተቻለም፡፡ ለምን ህብረቱ ተከፋፈለ? ለምን ሰፊ ድጋፍ አግኝቶ የነበረው ቅንጅት ተከፋፋለ፤ ተዳከመ ? ሴትየዋ ለምን ጫማዋን አሳመች? የበረከት ስምያንጓደኛና የትግል አፍራሽ ግለሰብ እንዴት የተቃዋሚ መሪ ተብሎ ቀጠለ ? የወያኔ ባለስልጣንሆኖ የወያኔን ከፋፋይ ፖለቲካ በመደገፍ በኢሕአፓና በአማራው ሕዝብ ላይ የዘመተ እንዴት የኢትዮጵያ አንድነትና የዴሞክራሲ አባወራ ነኝ ሲል ጎሽ ተባለ ?እነዚህንና መሰል ጥያቄዎች በማንሳቴ/በማንሳታችን በክብረ ነክ ተከሰናል፡፡ ይባስ ብሎ መአሕድ በብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ድርጅት ነው መባሉ ራሱ በፀረ ፕሮፌሰር አስራትነት አሁንም እያስወገዘ ነው፡፡ ሀቁን መናገር ስህተት ሆኖ ነው? የተወሰኑ ተጨፍነን አሞኙን ባዮች ደግሞ ኤ ኤፍ ዲ ወይም ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ የሚል ለሀገር የማይበጅ ጉድ በሻዕቢያ አዋላጅነትና በኦነግ የበላይነትብቅ ሲል ሳይቅሙ መርቅነው ይህን ፋይዳ ቢስ ስብስብ መጥፎ ነው ያልነውን ሲያወግዙን ነበር፡፡ ዛሬ ተሳስተን ነበር ብለው ይቅርታ መጠየቅ ይበዛባቸዋል? ኢትዮጵያዊ አይደለን ም ብለው ለደረቁ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያጨበጨቡና መጫወቻ ለመሆን የተነጠፉ ሁሉ ቢወቀሱ ሲያንስ ነው? ኤ ኤፍ ዲ ወይም ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለው ስብስብ ከስረ መሰረቱ ከኢትዮጵያ ጥቅም የተፃረረ መሆኑን ኢሕአፓ በማስረገጡ የደረሰበት ውግዘት የሚረሳ አይደለም፡፡

ዛሬ የዚህ ስብስብ ቀፎነትና ዋጋ ቢስነት ሲረጋገጥ ግን ስንደግፍ ተሳስተን ነበር የሚሉ ጥቂቶች ናቸው:: ዝም ዝምን መርጠዋል:: ዳግም መሰል ስህተተን ከመፈፀም የሚያግዳቸው የለም ብንል ስህተት አይሆንም::

ድርጅትና የተደራጀ ትግልን በተመለከተም በሕዝብ ትግል ደም የተገኘን ተመክሮ በመጥቀስ የቀረ ቡ ሀሳቦችን ረግጠው የነጎዱና የውሱን ጊዜ ሞቅ ሞቅ ዘላቂ ጥንካሬ የመሰላቸው ወይም የጠላትን የወያኔን የራሱን ይዘትና ጠባይ መረዳት ያቃታቸው በርካታ እንደነበሩ መታዘብም ችለናል:: ተጨባ ጩን ሁኔታ በማየትና ካለፈውም በማገናዘብ ትግሉን ለማጠናከርእንጣር ቢባል ገንቢ ሂስ በክብረነክ ተወስዶ ለምን ተናገራችሁ ወዘተ በሚል ውግዘቱ ሡተዥጎድጉዶ መደነባበሩ ሰፈነ :: ወደ ኋላ መለስ ብለን ያመለጡንን ወርቅ ጊዜዎች ወይም ዕድሎች ስንመረምር በአብዛኛው የፈፀምናቸው ስህተቶች ያለፈውን ተመክሮአችንን ተገንዝበን ቢሆን ኖሮ የማንደግማቸው ነበሩ:: ይህ ግን አልሆነም:: ትግሉ ም ተመክሮውን ሳልዘነጋው ወያኔ ሰለባ ሆኖ ተጎዳ::

- ኢሕአፓ ሻዕቢያንና የኤርትራን መገንጠል ደገፈ በለው ሲለፍፉና ሲከሱ ዓመታት ያሳለፉና ዛሬ ተሳስተን ነበር እንኳን ሳይሉ ያወግዙት የነበረው የሻዕቢያ አፈቀላጤ የሆኑ ከኢሕአፓም ከህዝብም ይቅርታ እስካልጠየቁ ደርስ ከሕዝብ ጎራ መገለል አለባቸው::
- ኢሕአፓ ቪቫ ዚያድ ባሬ ብሎ ጮኸ ፤ሶማሊያን ደገፈ ብለው በሀሰት ድርጅቱን ሲከሱ ከርመው ዛሬ ጠላት ያሉትን ሶማሊያ ደጋፊ ሆነው በዚያ በተበጠበጠ ምድር ያሉትን አክራሪዎች በጀግንነት ሲያሞግሱና የቅስጋዴን ነፃ አውጪ ነን ባዮችን ሲያደንቁ ስንሰማ በቅድሚያ ከሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ ሊባሉ ይገባል::

ትላንት የሕዝብን ኃይል ሲከፋፍሉ የነበሩ ዛሬ ግልብጥ ብለው የሕዝብ ወገን ነን ሲሉ ሆ ብሎ መቀበሉ በይቅርታ ጥየቃ ቢታጀብ ተገቢ ይሆናል:: ነጋ ጠባ በከሀዲዎች መገለባበጥ እየተመታን ወይ ጉድ ጉድ አደረጉን እኮ ማለቱ በጅልነት ያስፈርጀናል:: ዛሬ የትግሉ መድረክ ሊወገዙ በሚገባቸ ውና የሕዝብን ትግል ሲጎዱ በነበሩ አስመሳይ ሀገር ወዳዶች ተጠቧል:: በወሳኝ የታሪክ ጊዜ ብቅ ብቅ እያሉ የሕዝብን ጎራ ድፍርስርሱን አውጥተው ካበቁ በኋላ የሕዝብ ወገን ነን ሊሉ ሲቃጣቸው ማስቆም የሕዝብ ፈንታ ነው::

- በወያኔ አገዛዝ ላይ ትጥቅ ትግል የሞከረን ሁሉ ሲያወግዙ ተገልብጠው የትጥቅ ትግል አባወራ ነን ሲሉ የሚያምን ሁሉ ለሞኝነቱ ያስተማረውን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለበት::
- በወያኔ እስር ቤት አንድ እስረኛ የ 600 ገፅ መፅሀፍ ፅፎ ፤በምስጢር ወረቀቱን አውጥቶ፤ ዩጋንዳ አሳትሞ፤ ብዙ ሺ መፅሀፍ አስገብቶ በአደባባይ ሊሸጥ ወያኔ ይፈቅድለታል ብለው ያመኑ ካሉ በሬ መወለዱም ሀቅ ነው ቢባሉ የሚያምኑ ናቸውና እነሱም ለሞኝነታ ቸው ይቅርታ ከሕዝብ ሊጠይቁ ይገባቸዋል::

- የፍርሀት ታሪክ ያስመዘገቡ ግለሰቦች በተዓምር ጀግና የጦር መሪ ሆነው ለድል ያበቁናል ብሎ የሚያልም ሞኝ ካለም ለአስተማረው ሕዝብ ማፈሪያ ነውና ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባዋል።

በአጭሩ በሀገር የለም ዋዛ ነውና ሞኝነት አይፈቀድም። አለ ነገር፤ የሰዎቹም ሆነ የሴትየዋ አዝማሚያ አላማረም በተባለ በዚህ ፀሀፊ ላይ የደረሰው ውርጅብኝ ብዙ ነው። ዛሬ ግን ሀቁ በሙሉ ያውም ያልተባለ ያልተነገረ መሆኑ እየታየ ነው። ችግሩ ግን ያስተዛዝበናል ይህ ቀን ያልፍና የማለቱ ቅንጦት ሊኖረን አለመቻሉ ነው--ኢትዮጵያ በአደጋ ላይ ናትና። ድርጅቶች በሕዝብ ላይ የሚቀመጡ ልዩ አካሎች አይደሉም ወይም ሊሆኑ አይገባም። የድርጅት መሪዎችም ከዚህ ቀደም ልጠቁም ሞክሬ እንደነበረው ሕዝብ የሚሰግድላቸው ጣዖቶች ሊሆኑ አይገባም። የድርጅት መሪዎችን የምናከብራቸው የመሪነት ሚናቸውን ሊወጡ ከቻሉ ብቻ እንጂ እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ ብለው ስለተገበዙ ሊሆን አይደለም። ዘንድሮ ደግሞ ከሆነ የፈረንጅ ትምህርት ቤት ተምሯል የሚል ታርጋ ተሰጥቶኛልና መሪያችሁ መሆን ሲያንሰኝ ነው የሚሉ ብቅ ማለታቸውን አይተናል። በዚህም በዚያም ግን መሪዎቹን ለመውቀስ ሊኖረን የሚገባውን መብት ይነፍጉናል። የድርጅቶችንም ተመክሮ በሚገባ ለመመርመር እንዳንችል ያደርጉናል። ትግል ትግል ከተባለ ደግሞ ጉዳት የደረሰበት ድርጅት አገግሞና ተንሰራርቶ ወደፊት ለመጓዝ ቅርሱ የሆነውን ተመክሮው መገምገሙ ራሱ ትልቅ መሳሪያ ነው። በግለሂስ ተሀድሶ ይባል ነበር ያኔ በዚያ ዘመን። ኢሕአፓ ከቀይ ሽብር በኋላ በአራተኛው ጉባዔ ያካሄደው ይህንኑ ነው። ግለሂሱ ቢደረግም አሰረጫጨቱ ላይ ጥንቃቄ ባለመደረጉ የተጠበቀውን ግንባታ የተፃረረ ውጤት አመጣ ። ይህ እንዳለ ሆኖ ተመክሮን ግምገማ መደረግ ያለበት ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ብዙ ሕዝብ በዚህም በዚያም የደገፈው ቅንጅት አሁን ያለበት ደረጃ ለምን እንደደረሰ በሚገባ መመርመርና በዚህም ሂደት ተጠናክሮ ሊወጣ መቻል አለበት። ይህ ነው ቀናውና ተገቢው መንገድ እንጂ የድርጅትን ስህተት መጠቆም ሆነ የመሪዎችን ድክመት ማንሳት በወንጀል ደረጃ መታየት የሌለበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከሀዲንም ከሀዲ ማለት፤አንጃንም የስራውን ሰጥቶ አንጃ ማለት ስድብ ሳይሆን ጅብን ጅብ እንደማለት ነው።

ደም ያፈሰሰ ነፍሰ ገዳይ መቀጣት አለበት። ንስሀ ገብቶ ምህረት ሊሰጠውም ይቻላል። በለሆሳስና በዝምታ ከሕዝብ ጎራ ሊደባለቅ ግን ከቶም መቸም ሊፈቀድ አይገባም። አለበለዚያ ያለፉትን ስህተቶች እንደግምና ሀገራችንን የገደሉ በጫንቃችን ላይ ፊጥ ይላሉ። ዛሬ ነፍሰ ገዳዮች የፓልቶክ አስተናጋጅ፤ የታጋይ ተብዬ ድርጅት መሪ (ከቅስነግ እስከ ሌሎች) ወዘተ ሆነው ዝም ሊሉ ቀርቶ ከግድያ የተረፉትን ለመጨረስ ያጓራሉ። ከግድያ በመለስ ደግሞ የሕዝብን ትግል የጎዱና አልፎም ለባዕድ ያደሩትም ተሳስተን አጥፍተን ነበርን ሳይሉ ታጋይ፤የሕዝብ አለኝታ የሚባሉበት ልምድ መቆም አለበት። ሀገርና ሕዝብን የጎዱትን መሸለም፤ ማቀፍ ወዘተ ደግሞ ሀገርን የሚጎዳ ድርጊት መሆኑ ማንም ሊስተው አይችልም። ቻይ መሆን፤ በስልት መስራት፤

ስልጡን ፖለቲካ፤የጠላቴን ጠላት ወዳጄ ብሎ መስራት ብልህነት ወዘተ በሚል ሽፋን ባንዳን ማቀፉ ማብቃት አለበት። ንስሐ ካልቀደመ የሕዝብ ጎራ ይቆሽሻል፤ የሕዝብ ትግል በተደጋጋሚ ይጎዳል።

ታዲያ ይቅርታ እንጠየቅ ብንል ምን አጠፋን?